በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከአፕሪል 1-10 እና ከኤፕሪል 11-20/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

አፕሪል 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

**እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ** - 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 - 7 -

የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 - 7 -

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር - 7 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 - 7 -

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት ቀናት በምስራቅ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ፤ በደቡብ ምዕራብ እና  በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ  ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በልግ ዋናኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ፤ መካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እሰከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ  አግኝተዋል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ  30.5፤ በአርባ ምንጭ 20.6፤ በሃዋሳ  28.3፤ በቢሾፍቱ 55.4፤ በድሬ ዳዋ  52.1፤ በመተሃራ 68.6፣ 34.4፤ በአቦምሳ 96፣ 20.5፤ በአደሌ 20.8፤ በአንገር ጉቲን 27.4፤ በአርሲ ሮቤ 26.5፤ በአዋሽ አርባ 34.0፤ በበደሌ 42.7፤ በብላቴ 22.0፤  በቡኢ 43.3፣ 51.0፤ በቡሬ 30.0፤ በቦሬ 30.3፣ 36.2፤ በቡርጂ 54.0፤ በጨፋ 23.1፣27.5፤ በጭፍራ 52.2፤ በጭራ 59.5፣ 28.8፤ በዳሊፋጊ 54.2፣ 25.5፤ በዶሎመና 80.0፤ በጋቲራ 26.4 ፣25.6፤ በገለምሶ 24.5፣ 87.0፤ በቡሌ ሆራ 25.5፣ 25.7፤ በሆሳና 26.0፤ በሀረር 30.0፤ በገለምሶ 87.0፤ በጊኒር 30.0፤ በእምድብር 24.6 ፣68.8፣ 22.1፤ በጅንካ 20.8፤ በካቺሴ 28.3፤ በኮንሶ 33.5፤ በቁሉምሳ 30.2፣ 44.5፤ በማጀቴ 44.1፣ 57.2፤ በማጂ 20.0፤ በማሻ 30.6፤ በሜኤሶ 40.7፤ በኑራኤራ 72.6፤ በሰኮሩ 27.0፤ በቴፒ 21.5፤ በቴርጫ 21.8፤ በወራቤ 30.1፤ በያቤሎ 34.5፤20.0፤  በባቱ 71.5፣ 24.5፤ በቁሉቢ 46.1፤ በሂርና 48.1፤76 በግራዋ 40.0፤ በጨለንቆ 41.8፤ በኩርፋ ጨሌ 30.5፤ በደንገጎ 22.6፤ በቀብሪ በያ 38.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ምዕራብ ጉጂ፤ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ቡኖ በደሌ፣ጅማ እና ቦረና ዞኖች፤ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን እና ሊበን ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5፤ ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፣ ሁሉም የትግራይ ክልል ዞኖች፣ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊ፣ደቡብ እና ምዕራብ




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ጎንደር፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ዋህግምራ፣በህር ዳር ዙሪያ እና አዊ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ዶሎ፣ጀረር፣ኖጎብ እና አፍዴር ዞኖች፤ሁሉም የጋምቤላ ክልል፤የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ከአፋር ክልል ዞን 2፣1 እና 4 እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ኢሉባቦር፣ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች ላይ ከ5-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌእና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር ዞኖች፤ሁሉም የአፋር ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕካላዊ፣ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ ጎጃም፤ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ማዕከላዊ እና የምዕራብ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ፋፋን ዶሎ፣ኤረር እና አፍዴር ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ ዞን፤አዲስ አበባ፤ሀረሪ እና ድሬ ዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ።


በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35.0-43.4 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች እርጥበታማ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ (ካርታ 4)





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የላይኛው ተከዜ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን እና የግድቦችን የውሃ አቅም ከማሻሻል አኳያ አዎንታዊ ሚና ነበርው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው።


በመጪዎቹ አሥር ቀናት ለበልግ ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩና እንደሚስፋፉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 6፤ 7 እና 8)፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ምስራቅ ሸዋ፤ አዲስ አበባ፤ ምስራቅ አማራ፤ ሀረር፤ ድሬደዋ እና አይሻ፤ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ የምዕራብ ወለጋ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ ቦረና፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፤ የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚያዳርስ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛው እና የሰሜን




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል የአኛዋክ እና የመዥንግ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ክልል የአሶሳ፣ የማኦኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉ ትግራይ ዞን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 ሚኖረዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

በመጪዎቹ የኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 9) ።




ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ቀናት በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ሥፍራዎችን የሚሸፍን እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለበልግ ሰብሎች እና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት፤ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች፤ አርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትይህንንኑ ምቹ የአየር ሁኔታ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ዝግጅት ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅሥቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በተወሰኑ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ለዚሁ ችግር ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ተያያዥ ጉዳትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተገቢው የጥንቃቄ ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ. ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የላይኛው ተከዜ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን እና የግድቦችን የውሃ መጠን ከማሻሻል አኳያ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በአንጻሩ ግን በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር የሚችለው ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ጉዳት እንዳያሰከትል አስፈላጊውን የጥንቃቄ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et